# በመስቀሉ የከበሩ መስቀሉን ያክብሩ!

መስቀሉን ተሸክሞ ለቤዛ ዓለም የተገለጠው አማኑኤል ፈጣሪያችን፤ ቸር ከሚሆን ከባሕርይ አባቱና ይቅር ባይ ከሆን ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ክብርና ምስጋና ይግባው።የክቡር መስቀሉ የድኅነት ምልክትነት በኅላና በተረዳ ሁኔታ በሰዎች ልጆች በኩል ከመታወቁ በፊት በቅዱሳን መላእክት ከተማ የክቡር መስቀሉ የድል አድራጊነት ዓርማ ተገልጾ እንደነበር ይታወሳል።

አኀዜ መንጦላዕት ቅሩበ እግዚአብሔር ሊቀ መላእክት ሳጥናኤል፤ በዓለመ •መላእክት ጠብ ክርክር አስነስቶ እንደነበረ አይዘነጋም። ሳጥናኤል በክህደት አቅጣጫ ቆሞ ከታማኞቹ መላእክት ጋር ሙግት ሲገጥም፤ ለሁለት ጊዜያት ታማኞቹን መላእክት አሸንፏቸው እንደነበረ ይታወሳል። በሦስተኛው ሰልፍ ግን ሳጥናኤል ድል ሆነ። ምክንያቱም ቅዱሳን መላእክት የድል ዓርማ ቅዱስ መስቀል ከፈጣሪያቸው ተቀብለዋልና፤ በታማኞቹ እጅ የተያዘውን ክቡር መስቀል ዲያብሎስ ሲመለከትና ሲወድቅ አንድ ሆነ። በትግልና በብርታት ሳይሆን፤ በአምላክ ጥበብ ድልና ኃይል ለታማኞቹ የእግዚአብሔር ሠራዊት ሆነ። ስለዚህ ነው ዛሬ በቅዱሳን መላእክት ሥዕል ላይ፤ የድል አድራጊነት ዓርማ መስቀልን የምንመለከተው።

መስቀል በብሉይ ኪዳን የወንጀለኞች መቅጫ፣ የዕርግማንና የሞት ምልክት ሆኖ መቆየቱ አይዘነጋም። ዓመተ ፍዳ በዓመተ ምህረት ሲለወጥ፤ የዕርግማን፣ የፍርሃትና የሞት ምልክት መስቀል፤ የበረከትና የዕርቅ፣ የተስፋና የፍቅር፣ የሕይወትና የድኅነት ምልክት ለመሆን በቅቷል። በእርግጥ ደቂቀ አዳም መስቀል የሕይወት ምልክት መሆኑን በዘመነ ብሉይ ባይገነዘቡም፤ እስራኤላውያን በሙሴና በእግዚአብሔር ላይ በማንጎራጎራቸው በእባቦች በመነደፋቸው፤ ሙሴ በነሐስ እባብ ሠርቶ በመስቀል ላይ እንዲሰቀልና ያንን ያዩ ሁሉ እንዲድኑ በማድረግ አስቀድሞ ምሳሌ አሳይቷቸው ነበር (ዘኁል.፳፩÷፬-፱፣ ዮሐ.፫÷፲፬-፲፭) ክቡር ዳዊት በትንቢት መነጽርነት "... ከቀስት ፊት ያመልጡ ዘንድ ለሚፈሩህ ምልክትን ሰጠሃቸው" (መዝ.፶ ፱÷፬) ማለቱ ይታወቃል።

ይህም ትንቢት፤ መድኃኔዓለም ክርስቶስ በመስቀል ተሰቅሎልን ክቡር ሥጋውን ሲቆርስ፣ ክቡር ደሙን ሲያፈስ፣ በክቡር መስቀሉ ታላቅ ተአምራት ስለተገለጠ መስቀል የድኅነት ዓርማ መሆኑን ያስገነዝበናል። እንግዲህ የክቡር ዳዊት ትንቢትም ከሺህ ዓመት በኋላ ተፈጽሞ የመስቀሉ ምልክትነት እስራኤል ዘሥጋ ለተባሉት ለአብርሃም የሥጋ ልጆች ብቻ ሳይሆን እስራኤል ዘነፍስ ተብለን ለተጠራን በወልድ ውሉድ በክርስቶስ ክርስቲያን ለምንባል ለእኛም ተሰጠን።

በዘመነ ሐዲስ ደግሞ በክቡር መስቀሉ ምልክትነት፤ በረከት ያገኙ ቅዱሳን ቁጥራቸው እጅግ ብዙ ነው። የንግሥት ዕሌኒ ልጅ ታላቁ ቆስጠንጢኖስ ሲፋለሙት የነበሩትን የአሕዛብ ነገሥታት የመክሰምያኖስ ሠራዊት ድል ለማድረግ የበቃው ከሰማይ በተገለጠለት የመስቀል ዓርማ ነበር፤ "መስቀል አብርሃ በከዋክብት አስርገው ሰማየ፤ እምኩሉሰ ፀሐይ አርአየ" እንዲል በፈረሱ ዕንብርት፣ በጦሩ አንደበት በጋሻውም ላይ የመስቀልን ምልክት በመያዝ ዘመነ አሕዛብን በዘመነ ክርስትና ሊለውጠው በቅቷል። የመስቀል ኃይል መገለጥ ከላይ ከሰማይ ነው። ድልም የሚገኘው በመስቀሉ ኃይል እንጂ በሥጋዊ ኃይልና ብርታት አይደለም።

"ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች ተብሎ እንደተጻፈ፤ አበው ቀደምትና እናቶቻችን የመስቀሉን ዓርማ ለመፈለግ፣ በቃላት ሊገልጹት የሚያዳግት መስዋዕትነት ከፍለዋል። መቼም የእነ አፄ ዳዊትና የዘርዓ ያዕቆብን ታሪክ የሚረሳ ኢትዮጵያዊ ይኖራል ለማለት አንደፍርም። ግማደ መስቀሉን ወደ ሀገራችን ለማምጣት ያደረጉትን ጥረት ታሪክ ይዘክረዋል። ክርስቲያኖች ዛሬም ጭምር ግማደ መስቀሉ በክብር ወደሚገኝበት ወሎ ሀገረ ስብከት አምባሰል ግሸን ደብረ ከርቤ በመጓዝ፤ ከደዌ ሥጋቸው የሚፈወሱ "ልጄ ሆይ ኃጢአትህ ተሰረየልህ" በሚለው በረከት የሚጠቀሙ ወገኖች ቁጥራቸው በቀላሉ የሚገመት አይደለም። ዛሬም ቅድስት ቤተክርስቲያናችን የመስቀሉን ዓርማ በመያዝ፤ ለህሙማን ፈውስን እንደምትሰጥ በግልጽ የሚታይ ድርጊት ነው። ስለዚህ አበው ካህናት ጠላትን ድል የሚያደርጉበትን መስቀል በእጆቻቸው ይይዛሉ ምዕመናንም ይባርኩበታል። ተራውን ውኃ በመስቀል ባርከው በጠበል ፈታኙን ያርቁበታል። ማንም ሰው በተጨባጭ የሚፈጸሙትን ተአምራት ለመመልከት ወደ እውነተኛይቱ በር የተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ዘልቆ በመግባት ለማየት ይችላል። በሌላ በኩል ግን በጽድቅ ስምም የሚሠራ ኃጢአት እንዳሉ ምናልባት ባለማስተዋልም ሊሆን ይችላል የመስቀሉ ምልክት በክብር ሊያዝ ሲገባው እየተረገጠ መሆኑ ያሳስባል። ከዚህ አንፃር የመረረ ሀዘን የተሰማቸው አባቶች ድርጊቱን በመቃወም እያስተማሩ ነው። ጠንከር ብለውም የዘለፋ ቃል ለማሰማት የተዘጋጁም አሉ፤ በምህረት ፈንታ መቅሰፍት እንዳይመጣ ያሰጋናልና።

ድኅነት ዓለም የተፈጸመበትን የመስቀል ምልክት ክብሩን በመረዳት በክብር እንደማኖር መርገጥ መቅሰፍትን ሎጋበዝ ነው። በዓይናችን እንደተመለከትነው በብዙ አብያተክርስቲያናትና መኖሪያ ቤቶች ወለሉ ላይ የሚነጠፉ ምን ጣፎች የመስቀል ዓርማን ይዘዋል። መስቀሉም በመረገጥ ላይ ይገኛል። ይህም ድርጊት ሲፈጸመ "ሕዝቤ ዕውቀት ከማ ጣቱ የተነሳ ጠፍቷል።"(ሆሴ.፬÷፮) የሚለውን ኃይለቃል ያስታውሰናል። መስቀልን መርገጥ ታላቅ የማስተዋል ጉድለት ነው። የእውቀትም ማነስ ነው።

ለመስቀል ሊሰገድ ነው እንጂ ሊረገጥ አይገባም። ልበ አምላክ ዳዊት "እግሮቹ በሚቆሙበት ሥፍራ እንሰግ ዳለን።" ብሏል (መዝ.፻፴፩(፻፴፪)÷፯) ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ።(ገላ.፮÷ ፲፬) የመድኃኒታችን እግሮቹ የቆሙት በየት ነው ብለን ብንጠይቅ በመስቀል ላይ መሆኑን እንረዳለን። እንሰግዳለንም። "ብዙዎች ለክርስቶስ መስቀል ጠላቶች ሆነው ይመላለሳሉና አሁንም እንኳ እያለ ቀስሁ እላለሁ መጨረሻቸው ጥፋት ነው።" በማለት ቅዱስ ጳውሎስ አስተምሯል።(ፊል.፫÷፲፰) በቅድስት ቤተክርስቲያናችንም የጸሎት መጽሐፍ፤ በዘወትር ጸሎት "መስቀል ኃይላችን ነው፤ ኃይላችን መስቀል ነው፤ የሚያጸናን መስቀል ነው፣ መስቀል ቤዛችን ነው፣ መስቀል የነፍሳችን መዳኛ ነው። አይሁድ ይክዱታል እኛ ግን እናምነዋለን። ያመነው እኛም በመስቀሉ እንድናለን ድነናልም" ይላል። መስቀሉን የሚክዱስ ለይቶላቸዋል። መስቀሉን የሚረግጡ ግን ክርስትናቸው ያጠራጥራል። የመስቀሉ ምል ክት ከአማኞች ልብና ሕሊና እንዳይጠፋ አግባብ ነው። ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ "የማታስተውሉ የገላትያ ሰዎች ሆይ በዓይናችሁ ፊት ኢየሱስ ክርስቶስ እንደተሰቀለ ሆኖ ተስሎ ነበር፤ ለእውነት እንዳትታዘዙ አዚም ያደረገባችሁ ማን ነው? ይህን አንድ ነገር ብቻ ከእናንተ እማር ዘንድ እወዳለሁ" ብሏል። (ገላ.፫÷፩) እንግዲህ ነገረ መስቀሉን ዘወትር በልባችን ልናሰላስል ይገባናል። ታዲያ መስቀሉን በህሊናችን ካልተዘከርን እንደምን እናከብረው ዘንድ እንችላ ለን። በእግራችንስ ከተረገጠ ማክበራችን ወዴት ነው? የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት ለእኛ ለምንድን ግን የእ ግዚአብሔር ኃይል ነው እያለ።" በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበራችሁ፣ በጥምቀት ደግሞ፣ ከሙታን ባስነሳው በእ ግዚአብሔር አሠራር በማመናችሁ፣ ከእርሱ ጋር ተነሣችሁ። እናንተም በበደላችሁና ሥጋችሁን ባለመገረዝ ሙታን በሆናችሁ ጊዜ፣ ከእርሱ ጋር ሕይወትን ሰጣችሁ፤ በደላችሁን ሁሉ ይቅር አላችሁ፤ በእኛ ላይ የነበረውን የሚቃወመንንም በትእዛዛት የተጻፈውን የዕዳ ጽህፈት ደመሰሰው፤ እርሱንም በመስቀል ጠርቆ ከመንገድ አስወግዶታል፣ (ቆላ.፪÷፲፪-፲፬)

የኃይልና የድኅነት ምልክታችን የሆነውን መስቀልን መርገጥ ህሊናዊም ምክንያታዊም ድርጊት አይደለም። ወደ ባህር ማዶ ከተጓዙ ሰዎች እንደሚሰማው በአንድ አንድ የዓለም ክፍሎች ለሰይጣን ማደሪያ ቤት ተሠርቶ የሚ ገቡት መስቀሉን እየረገጡ መሆኑ ተረጋግጧል። እኛም መስቀል መርገጥን እንደስልጣኔ በመቁጠር ይሆን? የምንጓዝ በት አቅጣጫ ስህተት መሆኑን እናስተውል። በክቡር መስቀሉ የተረገጠው ሰይጣን ሌሎችንም ተንኮሎች እያስፈጸመ መሆኑ ታውቋል። በልዩ ልዩ ጫማዎች ላይም መስቀሉ እንዲረገጥ ለማድረግ ከሶሉ ውስጥ የመስቀል ዓርማ እ የተቀረጸ ነው።እንግዲህ በጌታችን መስቀል የተረገጠው ፈታኝ የድኅነት ምልክታችንን ለማጥፋት ማሰቡን እንገንዘባለን።

ጥንት በአይሁድ አድሮ የመስቀሉ ምልክት እንዲጠፋ አድርጎ የነበረው ክፉ መንፈስ ርኩስ ዓላማው ከሸፎበት በቅድስት ዕሌኒ አማካኝነት ከተቀበረበት ቦታ በቁፋሮ በጸሎት ዕጣን ምልክት መገኘቱ ይታወሳል። ዛሬ ደግሞ በጽድቅ ስም በሚሰራ ኃጢአት መስቀልን ማስረገጥ፤ በነፃነትና በዘመናዊነት ስም ክቡር ምልክቱን እንደተርታ ነገር መቁ ጠር በመጀመሩ ታላቅ የሆነው ግድፈታችንን ልናርመው አግባብ ነው። በዓመጽና በእልህ መንፈስ ብንጓዝ ግን በመ ስቀለ ክርስቶስ የተቀጠቀጠው ዲያብሎስን አባቴ፤ ሲዖል ገሃነመ እሳትን ቤቴ ናት እንደማለት የሚቆጠር ነው። የሰው ልጆች ፈጣሪያቸው በሰጣቸው ነፃ ፈቃድ ተጠቅመው ጠላታቸው ዲያብሎስን መከተላቸውን በሀዘንና ፀጸት እየሰማን ነው። እንግዲህ ምን እንላለን ፈታኝ የማረካቸውን ወገኖቹን አምላከ ምሕረት በቸርነቱ እንዲታደጋቸው እንጸልያለን። የመስቀሉን ክብር የተረዳን እኛ ግን፤ ሳናውቅ በስህተት የፈጸምነውንና የምንፈጽመውን የክህደት ሥራ አርቀን ስለ በደላችን ንስሐ እንግባ እንመለስ። ስህተታችንን ለማረም በፍቅርና በትሕትና እየጠራን ያለውን የመድኃኔዓለምን ድምጽ እንስማ። "ዛሬ ድምፁን ብትሰሙ ልባችሁን እልከኛ አታድርጉት" ተብሎ ተጽፏልና። ቸል ብንል ግን "የእግ ዚአብሔርን ሥራ በቸልታ የሚሠራ የተረገመ ይሁን" በሚለው ርግማን እንያዛለን። የናቁኝን እንቃለሁ. . . . ተብሎ ተጽፏል።

እሺ ብትሉ ለእኔም ብትታዘዙ የምድርን በረከት ትበላላችሁ፤ እንቢ ብትሉ ግን ብታምፁም ሰይፍ ይበላችኋል። (ኢሳ.፩÷፲፱) ስለዚህ የቤተክርስቲያን አባቶችና ምዕመናን በጉዳዩ ላይ ትኩረት ሰጥተው ባለማስተዋል የተነጠፉ መስ ቀል ያላቸው ምንጣፎችን በማንሳት በሁሉም አብያተክርስቲያናትና በቤታችን ጭምር ከመሬት ላይ ተነስተው በክብር እንዲቀመጡ ግድግዳ ላይ እንዲሆኑ እንዲደረግ በአክብሮት እናስታውሳለን።

ስብሐት ለእግዚአብሔር ወወላዲቱ ድንግል ወለመስቀሉ ክቡር።